## ሰንደቋ ህይወት ናት!



እንደ ጦጣ ወጥተህ የምትቦጫጭቃት፣
እንደ ቅርፊት ቀርፈህ መንገድ የምጥላት፣
ጉሬዛው ቢገባህ ሰንደቋ ህይወት ናት!

ጀግኖች በራስ አስረው ጠላት የደፉባት፣
ፋኖ ሞረሽ ብሎ የተጠራራባት፣
ስንቶች ደማቸውን እንደ እናት የጋቷት፣
የቅኝ ገዥ መቅሰፍት ሰንደቋ ነፍስ ናት!

ስንቱ አርበኛ ፋኖ የተሰዋው ለብሷት፣
ትውልድ መገናኘው ከፊት ያረጋት፣
በሰርግ በአውደ ዓመቱ የሚያውለበልባት፣
የሐዘን መግለጫው የደስታው መክሊት፣
የምትጉን ሲያወርዱት ታዳሽም ሲቀዱት፣
የማጠፋ እማትሞት ሰንደቋ ህይወት ናት።

ተፈጥሮ በሰማይ በህብር የሳላት፣
ምድሩ እንደ ቡቃያ ለጌጥ የሚለብሳት፣
ሰንደቋ ህላዊ ዘላለማዊ ናት።

የዓባይ ዙሪያ ኮርማ በሻኛው የሚያስራት፣
በአፋር ግመሎቹ በሩቁ እሚለዩአት፣
ጋሞ ጥበብ ሰሪ የሚያሽቆጠቁጣት፣
ዝንጀሮው ተገባህ ሰንደቋ ህይወት ናት።

ሐይቆች በታንኳቸው ሽብርቅ የሚሉባት፣
ወንዞቹ ሲወርዱ ዜማ እሚያዜሙላት፣
ተራሮች ተጫፍ ላይ የሚያውለበልቧት፣
ወፎች እያፉጫጩ የሚዘምሩላት፣
የውብ ዳር ሰንደቋ ዘንካታ እመቤት ናት።

ጽላት ጸበል ጻድቅ የሚሸፈኑባት፣
ቤተክሲያን ክዳኑ መርገፍ የሚያደርጋት፤
መስጊድ በግቢው ውስጥ ድምቅ እሚልባት፣
መቋሚያ ጸናጽል ማተብ የሚያጠልቃት፣
ከበሮ በገና ዋሽንት የሚለብሳት፣
ተምድር የማጠፋ ሰንደቋ መንፈስ ናት።

አባሆይ በጸሎት ሁሌ የሚያነሷት፣
እማሆይ በስስት እንባ የሚያጠጧት፣
ኮረዶች በወገብ ጥምጥም እሚያዞሯት፣
ጎረምሶችም በራስ እንደ ሻሽ የሚያስሯት፣
ወይዛዝርት በቀሚስ ዝንክት እሚሉባት፣
ጎልማሶች ተደረት ልጥፍ እሚያደርጓት፣
ልጆች አምባር ክታብ አልቦ የሚሰሯት፣
ሰንደቋ ሥጋችን ደም አጥንታችን ናት።

የሰይጣኑ ቁራጭ ጨርቅ ናት ስላላት፣
ባንዳ ሰላቶዎች አንይሽ ስላሏት፣
ትነድ እንዳይመስልህ ተእሳት ብትጥላት፣
ቀልጣ ታበራለች እንደ ወርቅ ያንገት ጌጥ።

አፍሪቃ በክብሯ በአርአያ የቀዳት፣
ጃማይካ እንደ ጣድቅ ሰግዶ የሚስማት፣
ቅኝ ገዥ እንደ ሹል ጦር በጣም የሚፈራት፣
ሰንደቋ ጠንካራ ወጀብ የማይወስዳት፣
የኖህ ድል ምልክት ቀስተ-ደመና ናት።

ትውልድ ለዘላለም የሚኖር ሲለብሳት፣
ጀግኖቹ ለክብሯ ደም የሚለግሷት፣
የነፃነት አርማ ሰንደቋ መንፈስ ናት!

በኮከብ አጉድፈህ መልኳን ብታጠፋት፣
ተምሰሶ አውርደህ በቦቴህ ብትረግጣት፣
ቦጭቀህ ቀዳደህ ተመንገድ ብጥላት፣
ታጥንት ተሥጋችን ቆርጠህ አታወጣት፣
ታርግ ትነሳለች ሰንደቋ ህይወት ናት!

ሰንደቋ ህይወት ናት!!
ህይወት ናት!
ህይወት ናት!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ጥር ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.